የሰ/መ/ቁ. 110901

ግንቦት 24 ቀን 2008ዓ/ም

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

ሙስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ሸምሱ ሺርጋጋ

አብርሃ መሰለ

አመልካች፡- አቶ ድጋፌ ታደሰ - ጠበቃ ሞገስ ናደው ቀርቧል

ተጠሪዎች፡- 1. ወ/ሮ ፍቅርተ ታደሰ ጠበቃ ክፍ አማከለው ቀርቧል

2. አቶ ወንድዬ ታደሰ - ቀርቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ለክርክር መነሻ የሆነው የአሁኑ አመልካች የውርስ ሃብት ይጠራልኝ ሲሉ ባቀረቡት አቤቱታ ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መናገሻ ምድብ ችሎት ነው፡፡ የአቤቱታው ይዘት ባጭሩ፡- አባታቸው አቶ ታደሰ አበበ ሐምሌ 11 ቀን 1974 ዓ.ም ከዚህ አለም የተለዩ ሲሆን ወራሽነታቸው የካቲት 11 ቀን 1975 ዓ.ም በመ/ቁ. 830/75 ያረጋገጡ መሆናቸው፤ ተጠሪዎች የወላጅ አባታቸው በጉለሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 8 ውስጥ የሚገኘውን የቤት ቁጥር 092 የሆነውን መኖሪያ ቤት ይዘው ስለሚገኙ የውርስ ሃብት ይጣራልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡

የአሁኑ 1ኛ ተጠሪ የቀረበውን አቤቱታ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ የውርስ ሃብት ይጣራልኝ ጥያቄ በፍ/ብ/ህ/ቁ.1000/1/2/ መሰረት የውርስ ሃብቱ በተጠሪዎች መያዙን ካወቁ ሶስት አመት ካለፈ በኋላ የቀረበ ስለሆነ በይርጋ ይታገዳል፡፡ በፍሬ ጉዳዩ ላይም የውርስ ሐብቱ ተመዝግቦ የሚገኘው በተጠሪዎች ስም እንጂ በአባታችን አይደለም፡፡ በዚህ ንብረት ላይ ከፍተኛ ንብረት አፍስውበት ይዘው እንደሚገኙ በመግለፅ አቤቱታው ውድቅ እንዲደረግላቸው መከላከያ መልሳቸውን አቅርበዋል፡፡

በመጀመሪያ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የአሁን 2ኛ ተጠሪ በክርክሩ ጣልቃ እንዲገባ በመፍቀድ ክርክር ካከሄደ በኂላ አመልካች አባታቸው ከሞቱ በኂላ በ1975 ዓ.ም ወራሽነታቸው ያረጋገጡት በፍ/ብ/ህ/ቁ.1000/1/ የተጠቀሰው የ3 ዓመት ይርጋ ጊዜ ሳያልፍ ስለሆነ የቀረበው መቃወሚያ በብይን ውድቅ በማድረግ፤ የውርስ አጣሪ በመሾም ከዚያም በውርስ አጣሪው የቀረበውን ሪፖርቱ ለህግና ለሞራል ተቃራኒ ስላልሆነ በማለት ተቀብሎ መዝግቦታል፡፡

ይህ ውሳኔ በመቃወም የአሁኑ ተጠሪዎች ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ቅሬታቸውን አቅርበዋል፡፡ ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት ፍርድ ቤትም አመልካች በስር ፍርድ ቤት ያቀረቡት የውርስ ይጣራልኝ ጥያቄ በፍ/ብ/ህ/ቁ.1000/1/ መሰረት በ3 ዓመት ይርጋ ይታገዳል በማለት የስር ፍርድ ቤት የተሰጠው ብይንና ውሳኔ በመሻር ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቤቱታው ቢያቀርብም በትእዛዝ ሰርዞታል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታም  የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስሕተት የተፈፀመበት ስለሆነ እንዲታረም በማለት የቀረበ ነው፡፡ የሕግ ስሕተት ተፈጽሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶችን ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡- ያቀረብኩት አቤቱታ ወራሽነቴን አረጋግጫለሁ በማናቸውም ጊዜ ውርስ ሀብቱን ለመካፈል የፍ/ብ/ህ/ቁ.1060 እስከ 1113 ባለው ህግ ስር የተሸፈነ ስለሆነ በይርጋ የማይተገድ እያለ ይታገዳል ተብሎ የተሰጠ ውሳኔ የተፈፀመው መሰረታዊ የህግ ስህተት በማረም የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ውሳኔ በማፅናት እንዲወሰንለት አቤቱታውን አቅርበዋል፡፡

የቀረበው የሰበር አቤቱታ በመመርመር አመልካች በወቅቱ ወራሽነቱን ማረጋገጡ አልተካደም ተጠሪዎችም የውርስ ንብረቱን በስማቸው በማዞር ካርታ ያሰሩት በ2004 ዓ.ም ከመሆኑ አንፃር የአመልካችን የውርስ ንብረት ጥያቄ በይርጋ ቀሪ ነው የመባሉን አግባብነትና የይርጋ ጊዜው መቆጠር ያለበት ተጠሪዎች ንብረቱን በሰማቸው አድርገው ከያዙበት ጊዜ ጀምሮ ነው ወይስ ሟች ከሞተበት ጊዜ ጀምሮ ነው የሚለውን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡

በዚሁ መሰረትም ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት በታዘዘው መሰረት ታህሳስ 14 ቀን 2008 ዓ.ም የተፃፈ 2 ገጽ መልስ አቅርቧል፡፡ አመልካች በበኩሉ ጥር 26 ቀን 2008 ዓ.ም የተፃፈ አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልሱን በማቅረብ ተከራክሯል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ እንደተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የሰበር አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመርነውም አመልካች ያቀረቡት አቤቱታ ወራሽነቴን አረጋግጫለሁ

በማናቸውም ጊዜ የውርስ ሀብቱን ለመካፈል የፍ/ብ/ህ/ቁ.1060 እስከ 1113 ባለው ህግ ስር የተሸፈነ ስለሆነ በይርጋ አይታገድም የሚል ነው፡፡ በተጠሪዎች በኩል ደግሞ አመልካች በፍ/ብ/ህ/ቁ. 1060 ተጠቃሚ የሚሆነው በወቅቱ ውርስ አጣርተው የዉርሱ ንብረት በወራሾች የጋራ ስም ተመዝግቦ ወይም ታውቆ የተቀመጠ የውርስ ሀብቱን እንከፋፈል ብሎ ለሚጠይቅ እንጂ የውርስ ይጣራልኝ ጥያቄ ለሚያቀርብ አይደለም፡፡ በስር ፍርድ ቤት የቀረበው የውርስ ሃብት ይጣራልኝ ስለሆነ አቤቱታና ሪፖርት በይርጋ ውድቅ መደረጉ በአግባቡ ነው የሚል ነው፡፡

የአመልካች አቤቱታ ተጠሪዎች የውርስ ሀብት ስለያዙ የውርስ ሀብት ይጣራልኝ የሚል መሆኑ በስር መዝገብ ተመልክቷል፡፡ ከቀረበው አቤቱታ በመነሳት ነው በመጀመሪያ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የውርስ ሀብት የሚያጣራ በመሾም ሪፖርት ሊቀበል የቻለው፡፡ ስለሆነም አመልካች የውርስ ይጣራልኝ ሳይሆን የውርስ ሀብት ክፍፍል ስለሆነ በይርጋ የሚታገድ አይደለም የሚል ክርክር፤ በስር ያልተነሳና ክርክር ያልተካሄደበት በዚህ ደረጃ መነሳቱ የፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 83 እና 329/1/ መሰረት ተቀባይነት የሌለው ነው፡፡

በሌላ በኩል የአመልካች አቤቱታ ይዘት ሲመረመር ለአቤቱታ መነሻ የሆነው የውርስ ሀብት ነው የተባለው ቤት ይዘው የሚኖርበት ወይም በኪራይ በሌላ አግባብ ተጠቃሚ መሆናቸው የሚያመለክት ክርክር የለም፡፡ አመልካች በስር ፍርድ ቤት ያቀረቡት ጥያቄ የወራሽነት እንጂ የውርስ ንብረት ክፍፍል ጥያቄ ባለመሆኑ በፍ/ብ/ህ/ቁ.1000/1/ መሰረት በሶስት ዓመት ዋጋ የሚታገድ ነው፡፡ ወራሾች ተለይተው የውርስ ሀብቱ ድርሻ ታውቆ ግን ደግሞ ክፍፍል ሳይደረግ የቆየውን የውርስ ሀብት በማናቸውም ጊዜ መጠየቅና በይርጋ የሚታገድ እንዳልሆነ ከፍ/ብ/ህ/ቁ. 1060 እና ተከታዮቹ ቁጥሮች መረዳት ይቻላል፡፡ በተያዘው ጉዳይ ግን ውርስ ማጣራት በመሆኑ ወራሾች መለየት፤ኑዛዜ መኖሩን አለመኖሩን፤ ዕዳ ጠያቂዎች መኖራቸው አለመኖራቸው፤ የእያንዳንዱ ወራሽ ድርሻ የሚታወቅበትና የሚጣራበት ነው፡፡ በመሆኑም የወራሽነት ጥያቄ አንድ ወራሽ በሌላ በወራሽነት የውርስ ሀብት በያዘው ሰው ላይ ክስ ሲያቀርብ ተፈፃሚነት ባላው የፍ/ብ/ህ/ቁጥር 1000/1/ ድንጋጌ ስር በተመለከተው በሶስት አመት ይርጋ የሚገደብ በመሆኑ ፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት እና ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በዚህ ረገድ የፈጸሙት መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት አለ ለማለት አልተቻለም፡፡ ስለሆነም ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ.107852 ጥር 15 ቀን 2007 ዓ.ም የተሰጠ ትእዛዝ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.151632 ህዳር 18 ቀን 2007 ዓ.ም በዋለ ችሎት የፌ/የመ/ደ/ ፍ/ቤት ውሳኔ በመሻር የተሰጠ ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ቁ.348/1/ መሰረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት ለተደረገው ወጭ እና ኪሳራ የግራ ቀኙን ተከራካሪ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/ተ